# እጅግ አጣዳፊ የተቀደሰ ፍልሚያ

መጋቢት ፴/ ፪ ሺህ ዓ.ም

ለክቡር ፡ አቶ መለስ ዜናዊ ፡ ጠቅላይ ሚኒስትር
ለክቡራን ፡ ለድርቅና ለጎርፍ አደጋዎች መከላከል ሞያ ያላችሁ.
የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆች ፡ በያላችሁበት
ከኮማንደር አሰፋ ሰይፉ ኢትዮጵያዊ ስደተኛ

# ወገንን ከዕልቂት ለማዳን

ኢትዮጵያችን በተደጋጋሚ በድርቅና በጎርፍ ምክንያቶች በአሳዛኝና : በሚያሳቅቅ እንዲያዉም በአሳፋሪ ሁኔታ ላይ መዉደ቟ን መጻፉ፡ ማንንም አላዋቂ ለማድረግ ሳይኾን የሚመጣው የበለጠ አስደንጋጭ መሆኑን ለማስጠንቀቅ ብዬ ነው። "በአሳፋሪ ሁኔታ፡ " ያልሁት በተደጋጋሚ ሲመላለስብን እጆቻችንን ለልመና ከመዘርጋት አልፈን ምንም ዓይነት የመከላከያ እንቅስቃሴ አለማድረጋችን ነው።
ኢትዮጵያችን አሁን ባለንበት ወቅት በዋጋ ንረት ምክንያት / ሰበብ፡- ልጆችዋ ተቃምሰው ማደራቸው እንኳን ከታምር ይቆጠራል፡-፡ መጨነቅ ፡- መሸበርን እንዲያዉም መርበድበድን የሚያመጣው፡ ግን፡- ነገ የሚያስከትለዉን አይቀሬዉን ሲያስቡት ነው።
በ "ሉላዊው ሙቀት" ምክንያት ኹለቱም ድርቅና ጎርፍ የሚያስከትሉት ዓለምን ከማነጋገር አልፎ አሳስቦታል። የኹለቱም ዉርጂብኝ ኃይላቸዉን የሚያበረቱት በአፍሪካ ላይ እንደኾነም ጠበብት አበክረው ያስጠነቅቃሉ፤፡ ይኽን ማስጠንቀቂያ ሰምተው የአፍሪካ መንግሥታትና ሕዝቦች ምን አደረጉ? በማለት ጎልጉልን ( ጉግልን) ስለኢትዮጵያችን ጎልጉል ብየ ብይዘው፤ " እንዴ ፡ ከየት ላምጣ? በቀ.ኃ.ሥ. ጊዜ የቀረዉን?!" ብሎ አፈጠጠበኝ፤፡ ያኹኑን የአምስት ዓመት ዕቅድ ባስፈለግ ያለፈዉን አገኘሁ. እዚያም ዉስጥ አይቀሬዉን ችጋርና ዕልቂት በተመለከተ ምንም አላገኘሁ። ርግጥ " የይድረሱልን ! " ዋይ ዋዩ አልገደደም። የተላያዩ የአገራችን ባለሥልጣኖችም የሰጧቸዉን መግለጫዎችንም ሳዳምጥና ስመለከት ያገኘሁት ባሉት የውሃ ሃብቶች ስለመጠቀም ብቻ ነው።

ስለዚህ እኔም የትውልድ እና የአገራዊ እንዲሁም የሰብአዊ ግዴታ ስላስጨነቀኝ፡-

# የተቀደሰው ፍልሚያው እነሆ !

የማይቀረዉን ግዳጃችንን ለኹለት ከፍለን ማየቱ ይበጅ መሠለኝ ፡-

# ድርቅንና ፦ ጎርፍን፦

በአሁኑ ጊዜ ስምንት ሚሊዮን ወገኖቻችን የምግብ ርዳታ እንደሚአስፈልጋቸው የዓለም የምግብ ድርጅት በቅርቡ አርድቶናል ( የማናውቀው ካለን) ያገር ስዎችና ስለአገራችን የሚያውቁት ስለ ረሃቡና ችግሩ እንዲሁም ስለ ገንዘቡ ግሽበት ሲናገሩ ቁጥሩን በጣም ከፍ ያደርጉታል። የዋጋ ንረቱን ሲያነሱማ

" ከጅ ነቃ-ነቃ ከግር ነቃ-ነቃ
እንዲህ አይደለም ወይ ቁምጥና ሲመጣ ? "

የተባለዉን በሥጋት ያሳስባሉ። ከዋጋ ንረቱ ጋር መነሳት የሚገባው የገቢ-የለሹና የጦም-ዐዳሪው ጉዳይ ነው። የሽሮንና የመሰሎቹን ዋጋ መጥቀስ ሳይሆን ማሰቡ የሚዘገንን ይመስለኛል ይኽ "ሉላዊ ሙቀት" የሚባለው ጒድ ከሰሜን አሜሪካ፦ ኒው ኦርሊአንስን ፦ ከደቡብ አሜሪካ ሰሜን አርጀንቲናን፦ ቦሊቪአንና ኤክዋዶርን ከደቡባዊ አፍሪካ እነ ሞዛምቢክን በእስያማ ስንቱ ተቆጥሮ !! ስሙን ሰምተን የማናውቀዉን ሱናሜን ስናስታዉስ ዋናው ጉዳይ፡ ከሞት የተረፉት የኹሉም አገሮች ተጠቂዎች እስካሁን ድረስ በመኖሪያ-የለሽነትና በተመጥዋችነት " ከሞተ በላይ ከቆመ በታች" ኑሮ ላይ መሰቃየታቸዉን በጥሞና እያሰላሰልን በየፊናችን ለወገናችን ማድረግ የሚገባንን ከማድረግ እንዳንቆጠብ ለማሳሰብ ነው።
ታድያ ኃይሉን አጠንክሮ ሲመጣ ምን አድርገን ልንጠብቀው ነው? አዳጋ አንለው ተመላልሷል፤- ዐላወቅንም አንል ዕናውቃለን! ለፅልቂቱና ለችጋሩ፤ መዘጋጀት ተቀዳሚ ተጠያቂው መንግሥት መኾኑ ባያጠያይቅም እኛ የአገሪቱ ሕዝብ ከደሙ ንፁሕ ነን ለማለት እንችላለን? እግዚአብሔርና ኅሊናችን እስካሉ ድረስ አንችልም ! ! !

የመፍትሄ አሳቦችን ሳቀርብ በሽርክቱ በግርድፉ መኾናቸዉን በቅድሚያ እንዲታወቅልኝ አሳስባለሁ። ማላሙ ቢቻልም ረጅም ጌዚ ስለሚያሻው ጊዜን መቆጠቡ ሕይወትንና ንብረትን ለማዳን ይጠቅማል ብዬ ነው እንጂ!

# ሀ -ድርቅ

ከድርቅ ጋር ከተዋወቅን ሳይሆን ሰለባው እየኾንን ስንኖር አያሌ ዘመናት ተቆጥረዋል። በመፍትሄ ደረጃ ግን ያየሁትና የሰማሁት አላገኘሁም። እኔ ከማስበው ጋር የሚገናኝ የሚቀራረብም እንኳን ባለማግኘቴ ሽርክቱን ባለሞያዎች ያልሙት ዘንድ ላቀርብ ተገደድሁ።

እስከ አኹን ሰዉም እንስሳዉም ያልቃል። የእንስሳው ሥጋውም ኾነ ቆዳው ሌሎች ከዚህ የሚገኙት አስተዋጽዖዎች ኹሉ ለሕዝቡ ጥቅም መዋላቸዉንም። እንዲያዉም ሕዝቡንና እንስሳዉን ለማዳን የተወሰደ ርምጃ ሳይሆን የተደረገ ጥንቃቄ ወይም ጥናት እንኳን

እንዳለ ያየሁትም የሰማሁትም የለም፤፡ እንኳን ከነበረ ካለም ለመታረም ደስተኛ እሆናለሁ.

# ለ- ጎርፍ

ጎርፍም በሕይወትና በንብረት ላይ በተከታታይ ያስከተለው ጥፋት በቀላሉ የሚረሳ አይደለም፤ እንዳይደገም ግን የተደረገው ከከንፈር መምጠጥ አልፎ መኖሩን እኹንም አላየሁም አልሰማሁም፦ ልክ እንደ ድርቁ ማለት ነው!! በዚህ መቀጠሉ ሕዝቡንም መንግሥትንም ከኅሊና እና ከታሪክ ተወቃሽነት በላይ ወንጀለኛ ስለሚያደርግ ኹላችንም ከዚህ ለመዳን የምንችለዉን እንሞክር ዘንድ ጭንቀት የወለደዉን ፍልምያ አቀርባለሁ።

# ግርድፍ የመፍትሄ አሳቦች፦

# ፩ ፦ ድርቅ

# ሀ - ማሸሻ

- ሲጀምር የሚታዩትን ምልክቶች ከአካባቢው ጠይቆ ልክ ያ ምልክት ሲታይ (የዝናቡን መቅረት ጭምር) በቀደምት ሰዉንና እንስሳዉን ከዚያ ማሸሽ፡
- ከባላግሩ በመማከር አርጀት-ከሳ ያሉትን ከባለቤቶቹ መግዛትና ማረድ
- ሥጋዉን ለምግብ ቆዳዉን ለሽያጭ የተረፈዉንም ሊጠቅም በሚችልበት ማዋል
- የተረፉትን ወደ ማሸሻው ሥፍራ ማጓጓዝ ከላይ፦ ማሸሽ ስል፦ ከተለመዱት የድርቅ አካባቢዎች ገባ ያሉ ምቹ ቦታዎች እየተመረጡ ለሕዝቡ መጠለያና ጉርሱ ለእንስሳትም መኖ አዘጋጅቶ መገኘት ማለቴ ነው ለዚሁም ትተራዎችን አስቀድሞ ማዘጋጀቱና መሙላቱ "ሠርጋኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ" ከሚባለው ያድናል

# ለ - ማስፈሪያ

በዚህ ሃሳብ ላይ ስለ ማስፈሪያ የቀረበው እስከማውቀው ድረስ ከዚህ በፊት ከተሞከሩት ወይም ከተደረጉት የተለየ ነው። ልዩነቶቹም እንደሚከተለው ይሆናሉ ፦

- የሠፈራ ቦታዎች ምርጫ በአረንጓዴነትና ባለመያዛቸው ብቻ ሳይሆን የአፈር ምርመራውና የአየሩ ተስማሚነት ለልማት ጠቃሚ መሆናቸው በጥናት ከተረጋገጠ በኋላ መሆን ይገባዋል

- ከነዋሪው ሕዝብ ጋር ምንም ዓይነት ቅሬታ እንዳይኖር በቀደምት ካገሩ ሽማግሌዎች ጋር መግባባት ያሻል
- ነዋሪዉም ኾነ ሠፋሪው ኑሮአቸዉን የሚጀምሩት እንደነበሩበት ሳይሆን በአዲስ መልክ ማድረጉ ይበጅ ያግባባ ይመስለኛል። ይኸዉም ፦
- የሠፈራው ቦታ በዐዋቂዎችና በባለሞያዎች ከተጠናና በአገሩ ሽማግሌዎች ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ሠፈራው ቅጥ በያዘ፦ በዘመናዊነትና በዘላቂነት ለሌላዉም አርአያ እንዲሆን ማድረግ ይጠቅም ይመስለኛል። ዘርዘር ሳደርገው፦ አሠፋፈሩ ከብት፡- ፍየልና በግን፦ እንዲሁም ዶሮ  አርቢዎችንና ገበሬዎቹን ለይቶ በየቀጣናው ማስፈርና አስፈላጊዎችን ሥልጠና  እንዲያገኙ  ማድረግና   ቶሎ የሚድርሱ ዘሮች (መካን  ያልሆኑ) በድጎማ....መለገስ  አይነተኛ  ለውጥ  ያመጣሉ የሚል  እምነት  አለኝ
- ለየባለሞያዎቹም "ለገበሬዎች  ለአርቢዎች  ማለቴ  ነው" በተቻለ ራሳቸዉን የማስቻያ መቆናጠጫ ይኾናቸው ዘንድ ፦ ለትልልቆቹ መሠረት ትምሕርት፦ ለልጆቹ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶች፦
- የጤና ጣቢያ ... ማዘጋጀት  ለኹሉም ማዕከል የሚሆን የዘመናዊ ከተማ ቅርጽ ኖሮት በሚያድግበት ጊዜ ብዙ ችግር እንዳይገጥመው ታቅዶ አንድ  ከተማ ዉስጥ ሊኖር የሚገባው ግልጋሎትን ሁሉ ያካተተ ዕቅድ በባለሞያዎች ማዘጋጀት፦

# ቤቶች መሥራትን በተመለከተ

አገራችን የሚሠሩት ቤቶች ጣርያና ግድግዳዎቻቸው በእንጨት  በመኾኑ አይቀሬዉን “ሉላዊ ሙቀትና”አጀቡን እንደሚያፋጥን ጠበብት ያስተምሩናል  ስለዚኽና የሠፈራ ቦታዎችን የዘመናዊ መልክ በማስያዝ  ወገናችን ከእንስሳ እጅግም ካልተለየ ኑሮው ከፍ ያለ ሕይወት እንዲቀምስ እዚያው አካባቢ በሚገኙ አሸዋና ገለባ (ባለሞያዎች) እንድሚወስኑት መስኮትና ማዕድቤት ያለው ኾኖ በብሎኬት ቢሠራ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ቤት ጓሮ ቢኖረው መልካም ይመስለኛል።  ለዚሁም  እንዳ  "መሸሻው" ጎተራ  ማዘጋጀቱ  ብልህነት  ይመስለኛል

# ጎርፍ፦

የጎርፍ ጉዳት በባላገሩ ብቻ ሳይኾን በየከተማዉም ነው;፡ ለየትኛዉም ቢኾን ስለተወሰደው የመፍትሂ ጥናትና ርምጃ የሰማሁት ስለሌለኝ እንደሌለ አድርጎ ማየቱን መርጫለሁ። ካለ፦ ከድፍረት አይቆጠርብኝ፤፡ በአማራጭ መውሰዱም ግን አይጎዳም።

ከተማዎች፦

ጎርፎች በተላያዩ ከተሞች አዲስ አበባ ጭምር ፦ በየዓመቱ ጉዳት እንዳስከተሉ ይታወቃል። የድሬዳዋው ግን እንደማውቀው ከሁሉም የከፋ ነው።  እሱን ለይቶ ለናሙና መውሰዱ ከታመነበትና ከተሠራበት ለሌሎቹም ያገለግላል የሚል ዕምነት አለኝ።

- በክረምት ወራት ድሬዳዋ ከደጋ በሚመጣ ፈረሰኛ ውሃ ለአደጋ የሚዳረገው ቦታ በበጋውደረቅ እንደሆነ ዐውቃለሁ። ይህ ከኾነ ሃሳቤም ተቀባይነት ካገኘ - ቁፈራው የሚጀምርበትም ቦታ በአገሬው ሰዎች ተመልክቶ ጥልቀቱና ስፋቱ በዐዋቂዎች ተወስኖ፦ በአስቸኳይ ሥራው ቢጀመር ከዘንድሮው ክረምት ዐደጋም የመዳን ዕድል ያለ ይመስለኛል
- ለዘንድሮው ለማድረስ ቦዩ ሲቆፈር ግራና ቀኙን በቁፋሮው አፈርም ሆነ አሸዋ መደቸር በፈጥኖ ደራሽነት ሲሆን ዐደጋዉን ማስቀረት አለበለዚያም ብዙ መቀነስ ይቻል ይመስለኛል
- የቁፋአሮዉን ሥራ ለመሥራት ያልበላ ክንድ የማይችል ወይም በተፈለገበት ጊዜ የማያደርስ ኾኖ ከታመነበት ቁፈራውን በዘመናዊ መሳሪያ አድርጎ ሥራ-ዐጡ ወገናችን ዳርና ዳሩን ቢደችር በልቶ ያድራል። ይኸም አሠራር በመመሪያነት ቢወሰድ የሠርቶ - ዐደሩን ቁጥር ያበረክታል።

- የወረደው ውህ ባክኖ እንዳይቀር ከከተማው ወጣ ብሎ ዐደጋ ከሚያደርስበት ዕልፍ ሲል የአሸዋዉም ሆነ የአፈሩ ቁፋሮ በኩሬ መልክ ቢኾንና ዉሃው አሸዋው ዉስጥ እንዳይሰርግ አፈሩንም ሆነ አሸውዋዉን በግድግዳነት ተጠቅቅሞ በ "ኮንክሪት" ቢሸፈን ግድቡ ዐቅም ተገኝቶ እስቲጠናከር ድረስ የተከተረው ዉሃ ለመጠነኛ የጓሮ አትክልት መስኖና ለሌላም ሊጠቅም ይችል ይመስልኛል።

# ከወንዞች ለሚደርሰው መጥለቅለቅ

መሠረተ አሳቡ ለድሬዳዋ የቀረበው መፍትሂ ዐይነት መሆኑ ይበጅ ይመስለኛል። ባለሞያዎቹ ይወስኑት።ለምሳሌ አዋሽን ብንወስድ፡ እንደማውቀው ዳሩን ዐልፎ ማሳዎችን ማጥለቅለቅ ይጀምር የነበረው በጅማ መንገድ በተጂና በቱሉቦሎ መኻከል ነበር። ይህ ወንዝ ዓመቱን በሙሉ የሚውርድ ስለኾነ፤ ባለሞያዎች በሚወስኑት ጥልቀትና ሥፋት መሠረት ከጎኑ በትይዩ ሌላ ቦይ ልበለው ወንዝ መቆፈር፤፡ባልተቆፈረው በኩል እንደሚያስፈልገው ተደችሮ የሞላው ዉሃ ወደ ተቆፈረው እንዲሄድ ማድረግ። እንዲህ ዐይነቱ ተግባር ዉሃው አካባቢዉን እንዳያጥለቀልቅ ይረዳል። ለወራጁ ግን መላ መምታት ያሻል።
ለእኔ የታየኝ ምቹ ቦታዎችን በመምረጥ በቀላሉ በከፊል እንዲከተሩ ኩሬዎች ማዘጋጀት;፡ የዚኽ ጥቅሙ የወራጁን ዉሃ መጠን በየርቀቱ ከመቀነስ በላይ የተከተረው ዉሃ ለእየአካባቢው የተለያዩ ጥቅሞችን የሚሰጡ ይመስለኛል። የሚፈራው ድርቅ ቢመጣም መኖራቸው ጉዳት አይኖረዉም ባይ ነኝ። ለዚኽ ዐይነቱ ሥራ ዝርዝሩን ለባለሞያዎች መተው ያዋጣል።
ሥራው መንገዶችን ማቋረጥ ማስከተሉ ዕውን ስለኾነ የድልድይ ሥራ ባለሞያዎችንም ይፈልጋል። አሸዋ ዉስጥ ሰርገው የሚቀሩትን ለድሬዳዋ በቀረበው አሳብ ወይም በተሻሻለ ዉሃዉን ለጥቅም ማትረፍ ሕይወትን ማትረፍ ይሆናል። ካላሳጠርሁት የሚአጥር ስላልመሰለኝ ወደ ሌላ ምዕራፍ ልሽጋገር።

# ደለሎች፦

አንዳንድ ግድቦች እንድያዉም ኩረዎች/ሃይቆች በደለል ተሞልተው እንደ ቆቃ ዓይነቶች ለከፋ አደጋ ቀን የሚጠብቁ ሲኾኑ ዓለማያ ግን በደለል በመሞላቱ የሐረርን ሕዝብ ለዉሃ-ጥም ዳርጎ አካባቢው ለምቶ ብዙ ሕዝብ ይተዳደርበት የነበረው ተግባር መና ኾኖ ቀርቷል፤፡ "ዱላ እስቲመጣ በክርን ያዝግሙ።" ነዉና የሕዝብ መረባረብ የማያስገኘው ጥቅም ስለሌለ ባለሞያዎች መላ ይምቱ!

# አፈጻጸም

እኔ በደጎባው ጽኁ ዕምነት ሥራው በታሰበው መልክ ዉጤት እንዲኖረው ከተፈለገ በነጻ ምክር ( እንዲፐንዳንት ቦርድ) መመራት ያስፈልገዋል;፡ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ያጤኗል ! ይኸም ምክር ( ቦርድ) የሚቋቋመው ለሕይወት አዳኝነት፦ ክብርን ከተመጽዋችነት በመውጣት ለመመለስ፦ ለኅሊና ነጻነት፦ ለወገናቸው ከሚደርሱት የታላቁ የኢትጵያ ሕዝብ ልጆች ፦እነዚሁም በዉሃ ጥናት፡ በድልድይ ሥራ በርሻ፦ በድልድይ፦በከተማ፦በትምሕርት፦ በመገናኛ፤ በዓለም-ዐቀፍ የገንዘብና የዕርዳታ ድርጅቶች በጤና ወዘተ ባለሞያዎች ስብስብ መመረጡ ላርኪ ዉጤት አማራጭ አይኖረዉም ከመንግሥት ጋር ያለው ቀጥታ ግንኙነት ከጠቅላይ ሚንስትሩና ከምክር ቤቱ ጋር ሲሆን ከሌሎች የመንግሥትና የዓለም-ዐቀፍ መሥሪያ ቤቶች፦ የበጎአድራጎት ተቋማትና ግለሰቦች ወዘተ የዕለት ተለት ተግባራቸዉን በዚህ ሥራ ላይ ከተሠማሩትና ስለዚህም ካጠኑት ጋር በመተባበርና በመደጋገፍ ቢሆን ይጠቅማል። ዝርዝሩን ምክሩ ሠርቶ ሕጋዊ ስበዐዊነቱን በክ. ጥ.ሚንስትሩ በኩል ባገኘ ጊዜ ይኾናል።

ምክሩ በዕውቀት በዳበሩና የሥራ ልምድም ባካበቱ ስለሚሞላ ወደ ተግባሩ ከመሮጥ በፊት ጥርት ያለ ዕቅድንና ቅደም-ተከተልን ያስጨብጡ እንደሚሆኑ እተማመናለሁ፡፤ ምክሩ ሲቋቋም አንዳንድ ጉዳዮችን ልጽፍላቸው ስለማስብ እዚህ ላይ ልግታው። አበክሬ ላስተዉስ የምገደደው ግን ተግባሩ በቅደም-ተከተል ሳይኾን ሲኾን ኹሉም ዐቅም ከፈቀደ አለበለዚያም አብዛኛዎቹ በትይዩ መተግበር ይኖርባቸዋል። ቅደም-ተከተሉ ሕይወትን ለማዳን ብቻ ቢኾን ይመረጣል።

ክቡር ጠ. ሚንስትሩን በአንክሮ ላሳስብ የምፈልገው፦ እንደሚያውቁት የዓለም የምግብ ድርጅት ጥር መጨረሻ ላይ ኢትዮጵያችን ለስምንት ሚሊዮን ልጆችዋ የምግብ ርዳታ እንደሚአስፈልጋት ተናግሯል። በመጋቢት መባቻ ላይ የዓ. መ. ማ. ዋና. ጸሓፊ አፍሪካ አረንጓዴ አብዮት ባስቸኳይ እንድሚአስፈልጋት አረጋግጠው አንዳንድ ዕቅዶችንም ገልጸዋል;፡ በዚያው ዕለት የአሚሪካ የችጋር አስቀድሞ አስጠንቃቂ ድርጅት የምግብ ርዳታ ፈላጊዎችን ቁጥር. ዘጠኝ ሚሊዮን አድርሶታል;፡ በዚሁ ዕለት የኢትዮጵያ የአይር ጠባይ ተመራማሪዎች፤ በበልግ ዝናብ ማነስ የተነሳ የዉሃ እጥረት እንድሚኖር አስጠነቅቋል፡፡ የሰብል እጥረቱን መንገሩን አልሰማሁም;፡ የእርሱ አለመናገር ግን ዕውነታዉን አይለዉጠዉም።

ይህን ሽርክት ግርድፍ ሃሳብ አልሞ ለዉጤት የሚያበቃ ስብስብ ለማግኘት አስቀድሞ የክቡርነትዎን ፈቃድና ሙሉ ተበባሪነትን ማረጋገጥ ስለሚያስፈልግ ይኸዉም "ብቅልጡፍ " በመገናኛ ብዙሀን የምስራቹ ይገለጣል ብዬ ላምን ዕወድዳለሁ። አሜሪካን ሁቨር ግድብን፥ ሂትልር ኦቶባኑን (ለመጥቀስ ያህል) የሠሩት ያገሮቻቸዉ ገንዘብ ተንኮታኩቶ ሥራ-ዐጦች ከተማዎችን ባጣበቡበት ጊዜ መኾኑ ታስቦ ለሕዝቡም ሥራ የሚያስገኝ መኾኑ አይጠፋዎትምና አዎንታዊ ቃልዎን በጉጉት እጠብቃለሁ። የአገር የወገን ጉዳይ ነዉና!!

የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለሞያዎች ወገኖቼ ሆይ፡ ዕውቀቱ፤ ፍላጎቱ፤ ጉጉቱ እያላችሁ በተለያዩ ምክንያቶች አገር - ወገናችሁን ሳታገለግሉ በመቅረታችሁ ምን ያኽል እንደምትንገበገቡ "ቂጥኛም ከዉርዴ" ሳይሆን ቂጥኛም ከቂጥኛም ስለሆነ ወገንን ለማዳን ባለሞያዎች ሁሉ ተባበሩ። ራስን ዝቅ አድርጎ " ምን እችላለሁ ? " ሳይሆን መቻል አለመቻልህን የሚነግርህ "ምክሩ" በመጀመሪያ ደረጃ ብዙ ዐዋቂዎች ያስፈልጉታል;፡ ሥራው በቅደም-ተከተል ሳይሆን ሁሉም በአንድ ጊዜ ተሠርቶ እንኳን ከዕልቂት ትንሽም ቢሆን ብናድን ከብዙ ዓይነት ወቀሳዎች እንድናለን;፡ መሪህንና የሥራ ጓደኞችህን መራጩ አንተው ትኾናለህ። ስለዚህ ወገንህን ለማዳን ክብርህን ለመጠበቅ ተሽቀዳደም:: ስለነዚህ ጉዳዮች ጥናት ያደረጋችሁትንማ አገራችሁ በማሾ ትፈልጋችኋለች!!

አገር ዉስጥም ሆነ ውጪ ያላችሁት ፈቃደኞች assefaseifu@hotmail.com
C/o ECB, 2A Lithos Rd., London NW3 6EF
በፋክስ. 44(0)20 7794 4116

የድረ-ገጽ (Website) ማዘጋጀት ዕውቀቱ ያላችሁ ተባባሪነታችሁን እንጠብቃለን